የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 4/0074/17
ቀን/Date JUN 0 3 2016

**በአባሪው ለተዘረዘሩት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ**

**በያሉበት**

**ጉዳዩ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመሪያ ቁጥር FXD/01/2024 አተገባበርን ይመለከታል፤**

እንደሚታወቀው ከዚህ ቀደም ለጉምሩክ ሥነስርዓት አፈጻጸም ሲባል አገልግሎት ላይ ሲውል የነበረው የውጭ ምንዛሪ ምጣኔ ብሔራዊ ባንክ ለጉምሩክ ኮሚሽን ለአንድ ሳምንት አገልግሎት ላይ የሚውል የውጭ አገራት ገንዘብ የምንዛሪ ተመን መሰረት አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር FXD/01/2024 አውጥቶ ከ22/11/2016 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን ባሳወቀው መሰረት በጉምሩክ ገቢና ወጪ ዕቃዎች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የውጭ አገራት ገንዘብ የምንዛሪ ተመን ባንኩ ካወጣው መመሪያ ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል፡፡

በዚሁ መሠረት በወጪ እና ገቢ ዕቃዎች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የውጭ አገራት ገንዘብ ምንዛሪ ተመን ለጉምሩክ ሥነስርዓት አፈጻጸም ተግባራዊ የሚሆነው በመመሪያው አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 5.3 መሠረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየዕለቱ ሥራ ላይ እንዲውል የሚያወጣውና ለተጠቃሚዎች ይፋ የሚያደርገው ተመን ይሆናል፡፡

ስለሆነም ባንኩ የሚያወጣውን ዕለታዊ የውጭ ምንዛሪ ተመን በኮሚሽናችን በኩል በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል፡-

1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣው መመሪያ ቁጥር FXD/01/2024 ተግባራዊ እንዲሆን ከተገለጸበት ከ22/11/2016 ዓ.ም ጀምሮ የተመዘገቡ ሰነዶች ባንኩ በየዕለቱ ተግባራዊ እንዲደረግ በሚያስተላልፈው የውጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል፣
2. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ተግባራዊ ከሆነበት ከ22/11/2016 ዓ.ም በፊት የተመዘገቡ ሰነዶች ሆነው የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት አጠናቀው መልቀቂያ ያልተሰጣቸው ዕቃዎች ከጉምሩክ መልቀቂያ አግኝተው ለነጻ ዝውውር በሚለቀቁበት ቀን ብሔራዊ ባንክ ባስተላለፈው የውጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት አስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጎ መስተንግዶ እንዲሰጥ፣



ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
ፖ.ሳ.ቁ. 2559
Email:- hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

CamScanner

3. ከ22/11/2016 በፊት ሥራ ላይ በነበረው የውጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት በራስ ማስላትም (self-assessment) ይሁን በኮሚሽኑ ማስተካከያ (Amendment) ተደርጎበት ቀረጥና ታክስ ከፍለው ለነጻ ዝውውር በ22/11/2016 ዓ.ም የተለቀቁ ዕቃዎች ላይ በ22/11/2016 ዓ.ም ብሔራዊ ባንክ ባስተላለፈው የውጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት አስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጎ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ይህ ሰርኩላር ከወጣበት ቀን ጀምሮ እንዲሰበሰብ፣
4. ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 2 ላይ የተቀመጡት አሠራሮች እንደተጠበቁ ሆነው ቀደም ሲል በሕግ አግባብ የተፈቀዱ ሆነው ከ22/11/2016 ዓ.ም ጀምሮ የጉምሩክ መልቀቂያ የሚሰጣቸው የክፍልፋይ ጭነቶች ጭነቱ በተለቀቀበት ቀን የብሔራዊ ባንክ ሥራ ላይ እንዲውል ባስተላለፈው የውጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት ቀረጥና ታክሱ ላይ አስፈላጊው ማስተካከያ ተደርጎ መስተንግዶ እንዲሰጥ እንዲደረግ፣
5. የጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በተራ ቁጥር 1፣ 2፣ 3 እና 4 ላይ የተመለከቱትን በጉምሩክ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በሲስተም ለማስፈጸም በማይቻልበት ጊዜ በልዩ ሁኔታ በኮሚሽኑ ወይም በመረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከል ኃላፊ ውሳኔ መሰረት በማኑዋል ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ መሰብሰብ ይኖርባቸዋል፣
6. ከብሔራዊ ባንክ በየዕለቱ የሚተላለፈው የውጭ ምንዛሪ ተመን በጉምሩክ ሲስተም ላይ በኮሚሽኑ የመረጃ ቴክኖሎጂ ማእከል በኩል ባንኩ መረጃውን እንዳሳወቀ ወዲያዉ መጫን ይኖርበታል፣
7. የዲክለራሲዮን አቅራቢዎች ከ22/11/2016 ዓ.ም ጀምሮ መዝግበው ለጉምሩክ የሚያቀርቡት ሰነዶች ላይ በየዕለቱ በሥራ ላይ የሚውለውን የውጭ ምንዛሪ ተመን መሰረት በማድረግ ትክክለኛ ቀረጥና ታክስ መክፈላቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፤
8. በመንገደኖች ጓዝ፣ የፖስታ ጥቅል እና በአየር ካርጎ የመጡ ለግል አገልግሎት የሚውሉ እቃዎች ከ22/11/2016 በፊት ሥራ ላይ በነበረው የውጭ ምንዛሪ መሰረት የጉምሩክ ስነስርዓት ፈጽመው በ22/11/2016 ለነጻ ዝውውር የተለቀቁ እና ከጉምሩክ መጋዘን የወጡ እቃዎች በአዲሱ የብሔራዊ ባንክ መመሪያ አተገባበር ምክንያት የሚፈለግ ቀሪ ቀረጥና ታክስ የሚሰበሰብ ይሆናል፣

ይህ አሠራር በሌላ እስከሚቀየር ድረስ ሁሉም የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች በጥንቃቄ ተግባረዊ እንዲያደርጉ እያሰሰብኩ የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ሥራ አስኪያጆች እና ምክትል ሥራ አስኪያጆች በጥብቅ ዲሲፕሊን እየመሩ ገቢው ሳይንጠባጠብ በአግባቡ እንዲሰበሰብ እንዲያደርጉ አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቀበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

**ግልባጭ፡-**

- ለጉምሩክ ሕግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለጉምሩክ ተቋማዊ ድጋፍ ዘርፍ
- ለጉምሩክ መረጃ ቴክኖሎጂ ማዕከል
- ለጉምሩክ ኮሚሽን ጽ/ቤት

**ጉምሩክ ኮሚሽን**

- ለገቢዎች ሚኒስቴር

ለገንዘብ ሚኒስቴር

ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ

**አዲስ አበባ**

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉምሩክ ቅጽ/ቤት
- ለአዋሽ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለሠመራ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሶሳ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለሀዋሳ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለታጁራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

<u>በያሉበት</u>

CS CamScanner